# የኢትዮጵያ
# ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)
# ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)

## አስቸኳይ በቂ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች

ህዳር 25/2015 ዓ.ም

### መግቢያ፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች በተደጋጋሚ ጊዜ በታጠቁ ቡድኖች በዋናነት በሸኔ ታጣቂ ቡድን ጥቃቶች እየተፈጸሙ መሆናቸውን በመግለጽ የፌደራል መንግስት እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከተው የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ይህንን ድርጊት እንዲያስቆም እና የሰዎችን ሰብዓዊ መብቶች እንዲያከብር እና እንዲያስከብር በተደጋጋሚ ጊዜ ባወጣቸው መግለጫዎች ሲወተውት ቆይቷል፡፡ ሆኖም ግን የፌደራል መንግስትም ሆነ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለጉዳዩ ተገቢውን በቂ ትኩረት በመስጠት ዘላቂ መፍትሔ ባለማምጣታቸው ጥቃቶች በታጣቂ ቡድኖች በዋናነት በክልሉ ላይ እየተንቀሳቀሰ በሚገኘው በሸኔ ታጣቂ ቡድን በተደጋጋሚ ጊዜ እየተጸመ ይገኛል፡፡ እየተፈጸሙ ያሉ ጥቃቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ሲሆን የተወሰኑ ቦታዎች ላይ በዋናነት በምዕራብ እና ምስራቅ ወለጋ ዞኖች ውስጥ በሚገኙ አካባቢዎች ላይ በተደጋጋሚ እየተፈጸሙ ይገኛሉ፡፡

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ውስጥ በሚገኘው የዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ህዳር 20 ቀን 2015 ዓ.ም የታጠቁ ቡድኖች ወደ ስራ የሚሄዱበትን መኪና በማስቆም ሴቶቹን እንዲሄዱ ከለቀቁ በኋላ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወንድ ሰራተኞችን አግተው መውሰዳቸውን እና እነዚህ ሰራተኞች ይህ ሪፖርት አስከወጣበት ጊዜ ድረስ አለመለቀቃቸውን ኢሰመጉ ከአካባቢው ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በተደጋጋሚ በሸኔ ታጣቂ ቡድን ጥቃት የሚፈጸምባቸው ምዕራብ ወለጋ ዞን ኪረሙ ወረዳ ሀሩ ቀበሌ እና ሌሎችም፣ ምስራቅ ሸዋ ዞን ጀጁ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ አካባቢዎች እና ምዕራብ ወለጋ ዞን ጉትን ወረዳ እንዲሁም ቱሉጋራ፣ ጃርዲጋ፣ አሞሮ እና ሌሎች አካባበዎች ላይ አሁንም ይህ ታጣቂ ቡድን በተደጋጋሚ ጥቃቶች እየፈጸመ መሆኑን እና ይህንን ጥቃት ለማስቆም ከፌደራል መንግስትም ሆነ ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የተሰጠ ዘላቂ መፍትሔ ባለመኖሩ ምክንያት የሚፈጸሙ ጥቃቶች መቀጠላቸውን እና በአካባቢው ላይ የሚኖሩ ሰዎች ስጋት ውስጥ መሆናቸውን ኢሰመጉ ከአካባቢዎቹ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡ ለእዚህም ማሳያነት በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ወለጋ ዞን ጊዳ ያና ወረዳ አንገር ጉትን ከተማ ህዳር 24 ቀን 2015 ዓ.ም ከንጋቱ 11፡30 ስዓት ጀምሮ ታጣቂ ቡድኖች ወደ ከተማዋ በመግባት በፈጸሙት ጥቃት በርካታ ሰዎች ህይወታቸውን እንዳጡ፣ ይህንን ድርጊት የፈጸሙት ታጣቂ ቡድኖች በከፍተኛ ሁኔታ የታጠቁ መሆናቸውን፣ ይህንን ጥቃት ተከትሎ በርካታ ቁጥር ያላቸው እና መሸሽ የሚችሉ ሰዎች ወደ ጫካ እንደገቡና አቅመ ደካሞች እና ህጻናት በከተማዋ ውስጥ መሆናቸውን ቤተሰቦቻቸው በጉትን ወረዳ የሚኖሩ ሰዎች በአካል ኢሰመጉ ቢሮ ድረስ በመምጣት ከተገኘ መረጃ እና ከአካባቢው ከተሰበሰበ መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን መተሐራ አካባቢ ወደ ጅቡቲ በሚወስደው መንገድ ላይ በሸኔ ታጣቂ ቡድን በተደጋጋሚ ጊዜ ጥቃቶች እየተፈጸሙ ይገኛሉ፡፡ በእዚህ መንገድ ላይ በሚፈጸሙ ጥቃቶች ሾፌሮች እና ሌሎችም ሰዎች እገታ እየተፈጸመባቸው ሲሆን ይህ ድርጊት በተደጋጋሚ ጊዜ በተለያየ መንገድ ለሚመለከተው አካል ቢገለጽም ምንም አይነት መፍትሔ ባለመበጀቱ ምክንያት እንደቀጠለ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በአካባቢው የሚኖሩ ነዋሪዎች እና መንገዱን የሚጠቀሙ የተሽከርካሪ ሹፌሮች እንዲሁም መንገደኞች ከፍተኛ ስጋት ውስጥ መሆናቸውን ኢሰመጉ ከአካባቢው ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ምክር ቤት ውስጥ በጉራጌ አስተዳደር ዞን የእዣ ወረዳን ወክለው የክልሉ ምክር ቤት አባል የሆኑት አቶ ታረቀኝ ደገፉ ህዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ልዩ ቦታው ቤቴል ተብሎ በ ሚጠራው አካባቢ ከሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው በመንግስት ፀጥታ ኃይሎች ተይዘው መወሰዳቸውን እና በወቅቱ ወዴት እንደተወሰዱ ሳይታወቅ

በምክር ቤት ያለመከሰስ መብታቸው ሳይነሳ ከተያዙ ከአራት ቀን ቆይታ በኋላ ህዳር 21 ቀን 2015 ዓ.ም ሀዋሳ ፍ/ቤት መቅረባቸውን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

ኢሰመጉ ከላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ የአካባቢዎቹ የጸጥታ ሁኔታ ሲፈቅድ ሰፋ ያለ የምርመራ ስራን በማከናወን ዝርዝር ዘገባን እንደሚያዘጋጅ ከወዲሁ ይገልጻል፡፡

## ተያያዥ የህግ ድንጋጌዎች፡

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 3፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳንም (ICCPR) በአንቀጽ 6(1) እና 9(1) ላይ እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት እንዳለው ያረጋግጣል። ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል-ኪዳኑ (ICCPR) የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2(1) እና 2(2) ይደነግጋል። የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች (ACHPR) አንቀጽ 4 ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት መብቱ ሊከበርለትና ሊጠበቅለት እንደሚገባና እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፈግ እንደማይችል ተመላክቷል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 14 “ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው” ሲል ይደነግጋል። በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 15 ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ ከተደነገገው ውጪ ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይችል በግልፅ ደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀጽ 16 ላይ ማ ንም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው ሲል ያስቀምጣል፡፡

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 13፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳንም (ICCPR) አንቀጽ 12 ላይ በአንድ አገር ግዛት ውስጥ በሕጋዊ መንገድ ያለ ማንኛውም ሰው በዚያ አገር ውስጥ በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት እንዳለው ይደነግጋሉ፡፡ የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች (ACHPR) አንቀጽ 6 ላይ ማንኛውም ሰው ነጻነቱና አካላዊ ደህንነቱ ተጠብቆለት የመኖር መብት አለው ሲል ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀጽ 17 እና 32 ላይ ማንኛውም ሰው የአካል ነጻነት መብት እንዳለው እና በነጻነት በፈለገው አካባቢ የመዘዋወር መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡
ምንም እንኳን ኢትዮጵያ አባል ሀገር ባትሆንም ሰዎችን አስገድዶ ከመሰወር ለመጠበቅ የወጣው ዓለም አቀፍ ስምምነት(International Convention for the Protection of All Persons from Enforced Disappearance) በአንቀጽ 1(1) ላይ ማንም ሰው ለአስገድዶ መሰወር ተጋላጭ መሆን እንደሌለበት በመደንገግ ይህንን ወንጀል የፈጸሙ አካላትን መንግስት በወንጀል ተጠያቂ እንዲያደርጋቸው ይደነግጋል፡፡

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 5 “ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ምክር ቤቱ ፍቃድ አይያዝም አይከሰስም” ሲል ይደነግጋል፡፡

## የኢሰመጉ ጥሪ፡

- የፌደራል መንግስት እና የኦሮሚያ ክልል መንግስት በኦሮሚያ ክልል በተደጋጋሚ እየተፈጸመ ላለው እና መቆሚያ ላጣው በታጣቂዎች በዋናነት በሸኔ ታጣቂ ቡድን የሚፈጸ ሙትን ጥቃቶች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በአስቸኳይ እንዲያስቆሙ፣
- መንግስት በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ውስጥ ከሚገኘው የዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ ህዳር 20 ቀን 2015 ዓ.ም ታግተው የተወሰዱ በድርጅቱ ውስጥ እየሰሩ የነበሩ ሰራተኞች ያሉበትን በማ ጣራት በሰላም እንዲያስመልስ እና የአካባቢውን ጸጥታ በማረጋገጥ መሰል ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ እንዲከላከል፣
- በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን መተሐራ አካባቢ በሚገኘው የጅቡቲ መንገድ ላይ በተደጋጋሚ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መንግስት በአስቸኳይ እንዲያስቆም፣

- በኦሮሚያ ክልል በተደጋጋሚ በሸኔ ታጣቂ ቡድን ጥቃት የሚፈጸምባቸው ምዕራብ ወለጋ ዞን ኪረሙ ወረዳ እና ጉትን ወረዳ እንዲሁም ምስራቅ ሸዋ ዞን ጀጁ ወረዳ እንዲሁም ቱሉጋራ፣ ጃርዲጋ፣ አሞሮ እና ሌሎች አካባበዎች እየደረሱ ያሉ ጥቃቶችን በማስቆም የፌደራል መንግስት እንዲሁም የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የሰዎችን በሰላም የመኖር፣ በህይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነት፣ በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት እና ሌሎችም መብቶችን እንዲያስከብር እና አንደ መንግስት ሀላፊነቱን እንዲወጣ፣
- በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ወለጋ ዞን ጊዳ ያና ወረዳ አንገር ጉትን ከተማ በታጠቁ ቡድኖች እየተፈጸመ ያለው ጥቃት አሁንም ባለመቆሙ የፌደራል መንግስት እና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በቂ ትኩረት በመስጠት የአካባቢውን ሰላም እንዲያስከብሩ፣ በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎችን ደህንነት እንዲያረጋግጡ እና ይህ ጥቃት በአስቸኳይ እንዲቆም እና መሰል ጥቃት ዳግም እንዳይከሰት ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎችን ሰብዓዊ መብቶች እንዲያስከብሩ፣

አዲስ አበባ ፤ኢትዮጵያ